# ‘የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
# ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር“
# በሚል ርዕስ

## በኘሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የተጻፈ
## መጽሐፍ ሲገመገም


ገምጋሚዎች

**ዳንኤል ዴሬሣ**

ቢ.ኤ. በታሪክ ኤም.ኤ በሶሻል አንትሮፖሎጂ

**ተሾመ ዱራ**

ቢ.ኤ በፍልስፍና ኤም.ኤ በሶሻል አንትሮፖሎጂ



ፊንፊኔ
ታህሣሥ 2000

# *“የአባ ባሕርይ ድርሰቶች ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር“*

# በሚል ርዕስ

## *በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የተጻፈ መጽሐፍ ሲገመገም*

*ገምጋሚዎች*

- ***ዳንኤል ዴሬሣ ቢ.ኤ. በታሪክ ኤም.ኤ በሶሻል አንትሮፖሎጂ*** E-mail :deressa – daniel @ yahoo. com
- ***ተሾመ ዱራ ቢ.ኤ በፍልስፍና ኤም.ኤ በሶሻል አንትሮፖሎጂ*** E-mail : teshdura @ yahoo. com

የኢትዮጵያ ኤምፓየርን ጉዱ-ጉዶች ተግባር ለዓመታት ብዙ ተናግረናል፤ አስተምረናልም:: በሕዝቦች ከርቸሌነት ሕልውኗን በአረጋገጠች ጉደኛ ኤምፓየር ውስጥ ኑረናል ፤ እየኖርንም ነው:: በአጭሩ ለማስታወስ ያህል በኢትዮጵያ ኤምፓየር ታሪክ ውስጥ የአቢሲኒያ ገዥ መደቦች እየተፈራረቁ የሕዝቦችን ብሔራዊ ማንነት ለማጥፋት ሞክረዋል:: የዲሞክራሲ ምድረ-በዳ በነበረች ኢትዮጵያ ሕዝቦች ለዘመናት የታገሉለት ዓላማ ዕውን ለማድረግ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ተገኝቶ የብሔር - ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ማንነት በሕገ - መንግሥት ለማረጋገጥ ጥረት በሚደረግበት በአሁኑ ወቅት፣ እንደ ትናንቱ ዛሬም የኢትዮጵያ ኤምፓየር “አንድነት“ በግድና በአንድ ወገን የበላይነት ወይም በሌላ አገላለጽ የሕዝቦች ሉዓላዊነትና ነፃነት በመጋፋት የበላይ ገዥነት እንደገና የሚመለስ መስሎአቸው “በአምቻ-ጋብቻ“እ ና “በመዋለድ“ በጥቅሉ በሚደስኩሩት የይስሙላ “አንድነት“ሽፋን ብሔራዊ ጭቆናን ለመመለስ እየሞከሩ ነው:: የሕዝቦች ብሔራዊ ማንነት ጨፍልቀው በኃይል ከአስገቡበት ብሔራዊ ምርኮ (National Enslavement) ወዲህ ባለው “የታሪክ“ መጽሐፎቻቸው /ድርሳናት/ እና “የአንድነት“ ሰበካቸው ብቻ ኢትዮጵያዊነትን ማለትም የእነሱ “ኢትዮጵያዊነት“ ምናባቸው ዛሬም ይቀርጻሉ:: የሕዝቦችን ትውልድ ከመነሻ ማወቅና ዕውቅና (Recognition) መስጠት አይዋጥላቸውም:: ለእነርሱ የራስን ብሔራዊ ማንነት መፈለግ “ቅብጠት“ ነው:: ለነርሱ የራስን ታሪክ ከእውነተኛ ምንጭ መቅዳት /መፈለግ/ “ኃጢአት“ ነው:: አንድ ሕዝብ ማንነቱንና ታሪኩን ከመነሻው ሳያውቅ በእነርሱ በጐ ፈቃድና“ፋብሪካ “ ካልታነፀ በእነርሱ “ውግዝ“ ነው:: እንግዲያውስ ታዲያ ዘረኛው ማን ነው?

መታወቅ የሚገባ አቢይ ጉዳይ ብሔርተኛነት በተፈጥሮው የሕዝቦችን አንድነት እንዳይመሰረት የሚጋብዝ እንዳልሆነ ነው። ብሔርተኝነት መሠረቱን በጠመንጃ /ነፍጥ/ ኃይል አገዛዝ ያደረገው ዘረኛ የባዕድ አገዛዝን እየታገሉ የጠፋውን ብሔራዊ ማንነትና ነፃነትን ማስመለስ እንደሆነ አያጠያይቅም። ይሁንና ሕዝቦች አሁን እየታገሉት ያለውና አጥብቀውም መታገል ያለባቸው ብሔራዊ ጭቆናን ( National Oppression) ነው።

በመሆኑም የዚህ ጽሑፍ አቅራቢዎች የራሱን ብሔራዊ ማንነትንና ነፃነትን የሚረዳ ሁሉ ኦሮሞንም ጨምሮ በዚህ ወሳኝ ወቅት (21ኛ ምዕተ-ዓመት) የኋላ- ቀርነት ሀበሻዊ ዘረኝነትና ጥላቻ (Abyssino-centric) አባዜ ያለቀቃቸው የኦሮሞን ብሔራዊ ማንነቱን በመዳፈር ዘመናውያን "ምሁር" ተብዬ አሮጌ መዝሙር ዘማሪዎች በኦሮሞ ላይ የሚደረድሩትን በመተቸትና ዕውነተኛ የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ እንዴት እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው።

በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የተደረሰውና በፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት መግቢያነት የተቋደሰ " **የአባ ባሕርይ ድርሰቶች ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር** " የሚለው መጽሐፍ ከነግሳንግሡ ሁለት መቶ ሃምሣ ገጾች አሉት። መጽሐፉን ሦስት አራት ጊዜ ደጋግመን አንብበነዋል። ለሦስተኛና አራተኛ ጊዜ ያነበብነው ግን ሂሳዊ ሀሳብ በመስጠት ነው።

ወደ ዝርዝር የሂስ አስተያየት ከመሄዳችን በፊት ግን የግዕዝ መረጃ ተብዬ በዚህ ጊዜ ለማንና ለምን እንደተጻፈ ከራሳቸው ከደራሲው ፕሮሰፌር ጌታቸው ኃይሌ መቅደም ሀሳብና ከፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የመግቢያ ቀዳሚ ሀሳብ በመነሳት ለማብራራት እንሞክራለን። ከሁሉም በፊት ግን አንባቢያን እንዲያውቁልን የምንፈልገው ከሁለቱ ፕሮፌሰሮች ነን ባዮች ጋር ዝምድናም ሆነ ጠላትነት የለንም።

እርግጥ የመጽሐፉን መግቢያ የጻፉት ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አንዳችንን የኢትዮጵያ ታሪክ ኮርስ አስተምረዋል። ብዙውን ጊዜ አዘውትረው ይጠቀሙ የነበረው መጽሐፍ ራሳቸው የጻፉት *"Church and State"* 1270-1527 የሚለው ነው። በዚህ "ዕጹብና ድንቅ" በተባለላቸው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ሲያነሱ፣ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ አንድም ቦታ ያነሱበት አጋጣሚ የለም። ዛሬ ደግሞ ፕሮፌሰር ጌታቸው በጻፉትና በግዕዝ በአስቀደሱት የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ ላይ ለመጻፍ መዳዳታቸው በጣም ይገርመናል። ያም ሆነ ይህ ሁለቱም

ዘመናዊ"ኘሮፌሰሮችና" ከነርሱ በፊት የነበሩ ጥንታዊ ደብተራዎች አንድ ዓላማ እንዳላቸው የእነኚህ ደራሲያን መጻሕፍት ያነበቡ ሁሉ በቀላሉ ይረዳሉ ብለን እናምናለን፡፡ ዓላማውም " ኢትዮጵያዊነት " " በአማራነት " ብቻ የሚገልጽ መሆኑንና የራስን ማንነት ማወቅ ደግሞ ሕዝቦችን የሚያቃቅር ነው /እንደ ኘሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ መጽሐፍ አገላለጽ/፡፡ የኦሮሞን ሕዝብ ባሕልና ታሪክ በማጉደፍ ኢትዮጵያዊነት በውዴታ ሳይሆን በግዴታ በመጫን "ኢትዮጵያዊነት" በአማራ የበላይ ገዥነት ለማቆየት ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ የተጻፈበት ምክንያት ከአሥራ አራት ዓመታት ወዲህ ከዚህ በፊት ባልተለመደውና ባልታየ ሁኔታ የኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ማንነታቸው፣ ባሕላቸውና ታሪካቸው በአደባባይ ይፋ ሆነው ብሔራዊ ንቃተ-ሕሊናቸው */National Consciousness/* እየዳበረ መምጣቱ ፣ እነርሱ በኃይልና በጉልበት ለገነቡዋት ኢትዮጵያ ሕልውና አደጋ መስሎ ስለታያቸው ሀቁን አድበስብሰው ይህንን እያደገ የመጣውን ብሔራዊ ንቃተ-ሕሊና ለማኮላሸትና ለማንኳሰስ " ኢትዮጵያዊነት" የሚለውን በውዴታ ሳይሆን በብሔራዊ አንድነት ሽፋን በማምታታት ሊያሳምኑና ማንነታችን በአንድነት ስም ሊያዘናጉን ይሞክራሉ፡፡

ነገር ግን ለደራሲው ኘሮፌሰር ጌታቸውና ተባባሪዎቻቸው /እንደ እነ ኘሮፌሰር ታደሰ ታምራትና ዶ/ር ዓለሜ እሼቴ ወዘተ አበክረንና አስረግጠን ለማለት የምንፈልገው ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ቤት እንድትሆን ለማድረግ ከተፈለገ ኢትዮጵያዊነትን መደራደር እንጂ በመጫን የሚመጣ አንዳችም ነገር የለም፡፡ መጫን ቅራኔንና አለመቻቻልን የሚያባብስ ካልሆነ በስተቀር የሚፈይደው ነገር የለውምና፡፡

ኘሮፌሰር! የታሪክ ምሁር ኖት አውቀው ግራ ለማጋባት ካልሆነ በስተቀር ኢትዮጵያ የሚለው ሥረወ - ቃል " ኢትዮጵስ" ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ፊታቸው የተቃጠለ (የከሰለ) ሕዝቦች" አገር ወይም በደፈናው የጠያይሞች (ጥቁሮች) አገር ማለት ነው፡፡ ይህ ስም በጥንታዊቷ ግሪክ ሥነ ፅሑፍ ማለትም በነሆመር ፣ ሄሮዱተስ ፣ ፐሊኒና ስትራቦ ሥራዎች ሲጠቀስ የኖረ ነው፡፡ ይህም በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ አፍሪካ ይኖሩ የነበሩትን ለጥንታዊ የኩሽ ሕዝብ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ይህንን ለኩሽ ሕዝቦች የተሰጠውን ስም ንጉሥ ኢዛና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግዛታቸው ውስጥ ለሚገኙ ሕዝቦች ተጠቅመውበታል፡፡

እርስዎ ግን ይህንን በጥንት ደብተራዎች የተፈበረከውን መረጃ ከመጠቀም በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ በኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ አስተባባሪነት

የላቀ ዕውቀት ባላቸው ምሁራን ተሳታፊነት "የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን" በሚል ርዕስ በኦሮምኛ ተጽፎ ወደ አማርኛና እንግሊዝኛ የተተረጎመውንና የታተመውን መጽሐፍ ቢያነቡ ደህና ግንዛቤ ያገኛሉ ብለን እናምናለን።

ለሁሉም በመግቢያ የታዩትን ሂሳዊ ሀሳቦቻችንን በዚህ እናብቃውና በአራት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በመመስረት ሂሳዊ ሀሳቦቻችንን ለመስጠት እንሞክራለን። እነኚህ መሰረታዊ ጉዳዮች 1ኛ የደራሲው ምንጮች 2ኛ የደራሲው ከወገንተኛነት ነጻ ያለመሆን 3ኛ የደራሲው የመረጃዎች አተረጓጎምና 4ኛውና የመጨረሻው የደራሲው ሀሳቦች ተአማንነት /*Validity*/ ናቸው።

## *1ኛ ፕሮፌሰሩ የተጠቀሙባቸው ምንጮች*

ፕሮፌሰሩ ከተጠቀሙባቸው ምንጮች ዋናውና መሠረቱ "ዜናሁ ለጋላ" የሚለው በታሪካዊ ምርምር ያልተደገፈ፣ ዝርዝር የራሱ ምንጮች የሌሉት ከታሪክነቱ ይልቅ ወደ መንፈሳዊነት ያጋደለ እንቶ ፈንቶ የአባ ባሕርይ ሥራ ነው። ይህ ጽሑፍ በክርስቲያን መንግሥቱ ደግ ደግ ሥራዎችና የኦሮሞዎችን ደካማ ጉኖች በማጉላት በኖስተልጂያ የተሟላ ጽሑፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ለምሳሌ በገጽ 25 ላይ ማየት እንደሚቻል ደራሲው የጉዱሩ ኦሮሞ የሚላቸው ከየትኛው ቤትና የኦሮሞ ጎሳ መሆናቸውን የማይገልጽ የእነ ሊቅ አለቃ ተክለ ኢየሱስ፣ አባ ባሕርይ እንቶ ፈንቶ ዳግም በማስተጋባት ኦሮሞ ከኢየሩሳሌም ፈለሰ የሚለው ፈጠራ ታሪክና በመሳሰሉት በመንተራስ ነው።

2ኛውና መሰረታዊ የመጽሐፉ ምንጭ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ የተጻፈው የአለቃ ታዬንና የአጽሜ ጊዮርጊስ የኦሮሞ ከውጭ መፍለስ የሚያበስርልን የተፈበረከ የሀበሻ ደብተራዎች የቅብብሎሽ ታሪክ ነው። " የአይጥ ምስክር ድንብጥ ናት" እንደተባለ ሁሉ ፕሮፌሰሩ ኦሮሞዎች በቅርቡ ከደቡብ የፈለሱ ናቸው የሚለውን የአጽሜንና የአለቃ ታዬን በደቡሽት ላይ የተመሰረተ "እውነታን" ከማስተጋባታቸው አልፎ ምንጩ በውል ያልተብራራውን የአለቃ ታዬን "የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ" የሚለውን መጽሐፍ በመረጃነት በመጠቀም ኦሮሞዎች በዛጉኤ ዘመነ- መንግሥት ወደ መሀል ኢትዮጵያ መምጣታቸውን ይናገራሉ። ለዚህም "የጻድቁ ገድል" የሚለውን ሥነ-መለኮታዊ መረጃን በእማኝነት ይጠቅሳሉ። ፕሮፌሰሩ ግን " የጻድቁን ገድል" ምንጮች ምን እንደሆኑ አንዳችም የገለጹት ነገር የለም። ይባስ ብሎም የአባ ባሕርይ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ተወዳዳሪ የሌለው የአንትሮፖሎጂ ምርምራዊ ድርሰት ነው ይሉናል። እንደ እኛ ግን አንዳችም አንትሮፖሎጂካዊ የምርምር ዘዴ፣ ሂደትና ውጤት አያሳይም።

ከዚያም በላይ አንድ የአንትሮፖሎጂካዊ ምርምር ሥራ ሊያሟላ የሚገባቸው የሕሊና ሚዛናዊ መለኪያ ይጐለዋል፡፡ ይህ የኘሮፌሰሩ መጽሐፍ በስድብና በስም አጥፊነትና በወንጀልኘነት ላይ ኦሮሞዎችን በመፈረጅ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ራሳቸው ኘሮፌሰሩን ጨምሮ የጥንቶቹም ሆኑ ዘመናዊ ደብተራዎች የቋንቋ አንትሮፖሎጂ ግንዛቤ ያላቸው አይመስለንም፡፡ ሆኖም ግን ጥንታውያን ደብተራዎች እነ አባ ባሕርይ፣ አጽሜ ጊዮርጊስና አለቃ ታዬ የመሳሰሉ የዚህን ግንዛቤ ባይኖራቸውም አይገርመንም፡፡ ዳሩ ግን "ዘመናዊ ምሁራን" ተብዬዎች የነዚህን ቀደምት ምንጮች ሲጠቀሙ ማብራሪያና ማስተካከያ መጠቀም ሲገባቸው በጥላቻ መርዝ ሽፋፍነው የጥንቱን ታሪካዊ ስህተት መድገማቸው የሚገርም ነው፡፡ ለምሳሌ በኘሮፌሰሩ መጽሐፍ ገጽ 105 ላይ የኦሮምኛ ቋንቋ በሴይጣን ማድሪያነት የፈለቀ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ይህ ፈጠራና ተራ ተረት ካልሆነ በስተቀር ምንም ዓይነት ኢትኖግራፊካዊና አንትሮፖሎጂካዊ ሞራላዊ ዕውነታ እንደሌለው በአንድ መሥመር እንኳን ኘሮፌሰሩ ማስተባበል አልሞከሩም፡፡ ስለዚህ ነው የጥንቶቹም ሆኑ የአሁኑ ምንጮች የፈጠራና የተረት ተረት ክምችቶች ናቸው የምንለው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኘሮፌሰሩ ከገጽ 106 እስከ 107 እነ ሰዮ፣ አቦኖ፣ ቱሜ ሌቃ ሃርሱና የመሳሰሉት ኦሮሞ ነገድ ውስጥ የገቡት በጥምቀት ነው ይላሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ኘሮፌሰሩ እንዲያውቁት የምንፈልገው ኦሮሞነት በጥምቀት አይገኝም፡፡ ጥምቀቱ በየትኛው ቦታ በየትኛው ክፍለ ዘመን ወዘተ እንደሆነ ቢያብራሩ ጥሩ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ጥምቀት የኦሮሞ ባህል ስለ አይደለ እዚህ ላይ የምንለው ነገር የለንም፡፡ ስሙን መናገር ያልፈለጉት ወይም ካላወቁ "ሞጋሳ" ወይም "ጉድፈቻ" ከሆነ ኦሮሞ ኦሮሞ ያልሆነውን ሕዝብ ወደራሱ የሚቀላቅልበት ወይም ወገን የሚያድርግበት በየትኛውም ዲሞክራሲ ውስጥ ያልታየ ውብና ድንቅ ሥርዓት አለው፡፡ በዚህ ላይ ብዙ ማለት አንፈልግም፡፡ በቅጡ ለመረዳት ከፈለጉ ግን "የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ" በሚል ርዕስ ባራንበራስ ጀቤሳ ኢጀታ በአማርኛና በኦሮምኛ የተጻፈውን መጽሐፍ አንብበው ሊረዱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እላይ በጥምቀት ወደ ኦሮሞ ገቡ ስለተባሉት ነገዶች ስንመለስ እነኚህ ከጥንት መሰረት ኦሮሞዎች ለመሆናቸው የዘር ግንዳቸውን /ሐረጋቸውን/ ዘርዝረው የሚናገሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ጉሣዎች በኦሮሞ አባቶች የዘር ግንድ ውስጥ ለመሆናቸው ለማረጋገጥ ከፈለጉ ደግሞ በአንዳንድ ገምጋሚዎች የሚሌኒየሙ መጽሐፍ ተብሎ የተሰየመውን 'የኦሮሞ ታሪክ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን" ቢመለከቱ /ቢያነቡ/ አውቀው ካልሆነ በስተቀር የተወናበዱበትን ሊያስተካክሉ እንደሚችሉ እናምናለን፡፡

## *2ኛ ከግል ፍላጐት /Value Free/*

በመጽሐፉ ገጽ 16 መጨረሻ አንቀጽ ላይ እንዲህ የሚጠቀስ አለ:: "…የዛሬዎቹ ኢትዮጵያን በነገድ ሲጣሉ ለሕዝቡ አንድነት ባለኝ ምኞት ….ያልተሟላ እራስን ማሟላት ….የአየሁትን ለመመስከር ነው" ይላሉ:: ደራሲው እዚህ ላይ ሕዝብና ነገድ በሚባሉ ሁለት ጽንሰ- ሀሳቦች መካከል ያለውን ልዩነት ለይተው የሚያውቁ አይመስሉም:: ወይም አውቀው ላለመጥቀስ ፈልገው ይሆናል:: ዳሩ ግን በአጭሩ ለማስቀመጥ ኦሮሞ ብሔራዊ ሕዝብ /Nation/ እንጂ ነገድ አይደለም:: ዛሬ ከሠላሳ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ ነገድ አድርጐ ማስቀመጥ ሕጋዊ፣ ሞራላዊና ዕውነታዊ መሠረት የለውም:: በእኛ እምነት ነገድ አናሳ የሕዝብ ቅርንጫፍ ወይም ክፍል ነው:: ሰፋ ያለውን ትርጉሙን ለማወቅ ደግሞ እንዲመራመሩበት ወንድማዊና ምሁራዊ ምክራችንን እንለግስዎታለን:: የሕዝቦች አንድነት በምኞት ብቻ አይመጣም:: እውነተኛ አንድነት ለማምጣት በዕኩልነት፣ በመፈቃቀር፣ በመፈቃቀድና በመቻቻል ላይ የተመሠረተና ተግባራዊ መተሳሰብና መተዋወቅ በብሔራዊ ማንነታችን ላይ መግባባት ሊኖረን ይገባል :: ኦሮሞ ሆኖ ኢትዮጵያዊ መሆን ይቻላል:: ነገር ግን ኢትዮጵያዊ ለመሆን ኦሮሞነታችን ማጣት የለብንም:: ማንነታችን መናገር ደግሞ ሌሎችን የሚያስከፋ ሆድ የሚያባብስና የሚያጣላ መሆን የለበትም:: ደራሲው ማንነታችንን መናገር ማሳወቅ የነገድ ጥላቻ ያስከትላል ይላሉ:: ይህ አስተሳሰብ ኢ-ሳይንሳዊ ከመሆኑም በላይ ለኢትዮጵያዊነት መሠረት ሊሆን አይችልም:: ኘሮፌሰሩ ግን የግል ፍላጐታቸውን በዚህ አጋጣሚ ለማንጸባረቅ የሞከሩ ይመስላሉ::

በመጽሐፉ ከገጽ 63 ስከ 93 በግዕዝና በአማርኛ ትርጉም የተቀመጠውን የኦሮሞ ንዑሳን ጐሣዎች ዝርዝር ተመልክተነዋል:: የግዕዙ እስክሪኘት ቀጥተኛ ትርጉም ከሆነ በሁለቱም ቋንቋዎች የሰፈሩት የኦሮሞ የዘር ግንድ ከፊሉ ልክ አይደለም:: ከፊሎቹ ደግሞ የኦሮምኛ ቃሎች አይደሉም:: የሰው ስምና የሉባ ስሞችም ተመታተዋል:: ስለዚህ ተአማንነት የላቸውም:: ከገጽ 91-93 ላይ የሠፈረው የኦሮሞ ሕብረተሰባዊ የሞያ ድልድል ስሞቹ በከፊል ልክ አይደሉም:: ከፊሎቹ ደግሞ በኦሮሞ ባህል ውስጥ የሌሉና የማይታወቁ ናቸው:: ለምሳሌ ከብት የሚነዱ 10 ሰዎች የወል መጠሪያቸው "ጣውቱ" ይባላሉ ይላል:: በውሸት ተፈብርኮ ካልሆነ በስተቀር "ጣውቱ" የሚል የወል ስም ምንም ዓይነት ሥረወ-ቃል /Etymological/ ማህበራዊና አንትሮፖሎጂካዊ መሠረት የለውም:: ስለዚህ ነው ኘሮፌሰሩ ዋና ምንጭ ያደረጉትና የአወደሱት የአባ ባሕርይ መጽሐፍ በምርምር ያልተደገፈ ተአማንነት የሌለው የተረት ተረት ነው የምንለው::

በሌላ በኩል ደራሲው " ጋላ" ለሚለው ቃል ስያሜ የሰጡት ትርጉም ጥንታዊ የቤተ-መንግስት ደብተራዎች እንደ አለቃ ታዬና አጽሜ ጊዮርጊስ ከሰጡት ትርጉም ብዙ ልዩነት የለውም:: ይልቅስ የተሳሳቱት ነገር ቢኖር የአማርኛ መዝገበ ቃላታቸው ' ጋላ' ለሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሰጠውን ልብ አለማለታቸው ነው:: 'ጋላ' ማለት "አረመኔ"፣"ክርስትና ያልተነሳ" "ጨካኝ" ወዘተ ተብሎ ተተርጉሟል:: ለስያሚውና ለትርጉም ሰጪው ዘረኞች የኦሮሞ ሕዝብ በቂ የአጸፋ መልስ ቢኖረውም የዘረኝነት አባዜና የጥላቻ መርዝ በተፈጥሮ ስላልተጠናወተውና በራሱ ስለሚተማመን ከማንኛውም ኢ-ሰብአዊ ድርጊትና ግፍ ይታቀባል:: ስለዚህ የኦሮሞ ሕዝብ በጨቋኝ ገዥ መደቦች 'ጋላ' ተብሎ የተሰጠውን ስም አይቀበልም:: ይህንን ታሪካዊ ዕውነታ በመረዳትም ከደርግ እስካሁን ያሉት መንግሥታት ኦሮሞ የሚል ስም ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ የሕዝቡ የወል መጠሪያ ስም ሆኖ ይገኛል:: ነገር ግን ደራሲው የታሪክ ጎማን ወደ ኋላ በመሳብ 'ጋላ' የሚለው መጠቀማቸው ከትምክተኝነትና ከሕዝቡ ንቀት የመነጨ መሆኑን አንባቢያን ሊረዱ ይችላሉ::

እዚህ ላይ ሌላ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ጉዳይ ደራሲው በቋንቋ ምንነት ላይ ያላቸው ግንዛቤ ነው:: በገጽ 101 ላይ "... ቋንቋ እንደልብስ የሚቀያይሩ ስለሆነ "...ካሉ በኋላ ቋንቋ የማንነት መገለጫ እንዳልሆነና የሰዎች ማንነት በቋንቋቸው መገለጽ የለበትም ይላሉ:: እኛ ግን የምንለው ቋንቋ ከማንነት መገለጫ አንዱና ዋነኛው ነው እንላለን:: እርግጥ ቋንቋ የሚያድግና (Dynamics) በየጊዜው በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች ለተለያዩ ዓላማዎች መጠቀሚያ ሊውል ይችላል:: ነገር ግን ለአንድ ሕዝብ የማንነቱ መገለጫ የሆኑት ሌሎች ቁሳዊና ኢ-ቁሳዊ ሪዮተ ዓለሙና ባህሎቹ የሚገለጹት በቋንቋ ነው:: ደራሲው ሰው በቋንቋው መናገር፣ መሥራት ፣ መጻፍ፣ መገናኘትም ሕዝቦችን እንደ መከፋፈል አድርገው ቆጥረውታል:: ይህም ፍላጐታቸው በትምክህት የተሟላ ገለልተኛ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው::

በገጽ 102 'ላይ 'ጋላ' የሚል መጠሪያ ስም ስድብ ነው ወይ? በሚል ንዑስ ርዕስ ሥር 'ጋላ' የሚል ስም ገለልተኛ የሕዝብ መጠሪያ ስም ነውና ትክክለኛ ነው ብለው ሊያሳምኑን ይሞክራሉ:: ነገር ግን 'ጋላ' የሚለው መጠሪያ ስም በአማርኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ የተቀመጠውን /የሰፈረውን/ እላይ ስለተጠቀሰ እንደገና አንመለስበትም:: ግን ትክክለኛና ጤናማ ሕሊና ያለው ሰው በአንድ በኩል አንድነትን እየተመኘና እየደሰኮረ በሌላ በኩል ሕዝብን በማይመለከተው ስም እየሰየመ ስድብ አይደለም ቡራኬ

ነው ሊሰን አይችልም። ስለዚህ ነው መጽሐፉ ገለልተኝነት፣ ሚዛናዊነትና ተአማንነት የጐደለው ነው የምንለው።

ሌላው ኦሮሞ መባል "... ተገንጣይ ኦሮሞችን ስለሚያስታውሰን ጥንቃቄ ይወሰድ" ይላሉ። ይህም ደራሲው የፖለቲካ ወገንተኛ መሆናቸውን ቁልጭ አድርጐ ያሳየናል። ኦሮሞ ለሚለው ስያሜና ግንዛቤ መሪር ጥላቻ ስለ አላቸው ከመገንጠል ዓላማ ጋር በማያያዝ ስሙ "ጋላ" በሚል እንዲቀጥልላቸው የሚፈልጉ ናቸው።

በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በመስሎቻቸው የተፈበረከውን "የክርስትና ስም" መልሰው ሊያጐናጽፉን ይዳዳሉ። ይህ ደግሞ አይቻልም። ኦሮሞ ኦሮሞነቱን የማንነቱን መገለጫ የሕልውና አሻራ የባህሎቹን ማስጠበቂያ የሆኑትን ለማስነጠቅ ለስምምነትና ለድርድር የሚያቀርብበት ጊዜ አብቅቷል።

## *3ኛ የደራሲው የምንጮች አተረጓገም/Interpretation/*

የመጽሐፉ ሁለንተናዊ አገላለጽ ወገንተኝነት እንደሚያፀባርቅ ከላይ በመጠኑ ጠቅሰናል። ፕሮፌሰር ጌታቸው 'ጋሎች' በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማዕከላዊ ኢትዮጵያን ወረሩ ብለው የአባ ባሕርይንና የመሰሎቻቸውን ድስኩር ይደሰኩራሉ። በዚህ ላይ ደራሲው አንድ ዋና መሠረታዊ ጉዳይ እንዲያውቁ እንፈልጋለን። ይኸውም ኦሮሞ እንደ ማናቸውም የኩሽ ሕዝቦች ኢትዮጵያን ጨምረው በምስራቅ አፍሪካ እየኖረ ያለ ሕዝብ ነው። ከየትም አልመጣም። ጥንታዊ የአፍሪካ ቀንድ ነዋሪ እንደ መሆኑ መጠን የታሪክ ዘመናት በውል ካልታወቀበት ጊዜ ጀምሮ እየኖረ ይገኛል። ሴማውያን ማለትም ሰባውያን፣ አጋዚያንና ሀበሻት የተባሉ ሕዝቦች ቀይ ባህርን ተሻግረው ሲመጡ /በራሱ በደራሲውና በተባባሪያቸው የታሪክ ግኝት ተብዬው መሠረት/ እስከ ሰሜኑ ኢትዮጵያ ሰፍረው ይኖር የነበረውን ኦሮሞም ሆነ ሌሎች የኩሽ ሕዝቦች ሙሉ በሙሉ ለቀው አልወጡም። ስለሆነም ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ አልፈው እስከ ሰሜን ጫፍ ድረስ ኦሮሞም ሆነ ሌሎች የኩሽ ሕዝቦች መኖራቸው የአገው፣ የቤጃ፣ የብሌን እ ንዲሁም የራያና የአሴቦ ፣ የወሎ ቦረና ኦሮሞዎች ሕያው ምስክሮች ናቸው።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የገዳ ተሀድሶ /Gada Renaissance/ የተከናወነበትና የመደ ወላቡ አካባቢ ኦሮሞች ቦረናና ባሬንቱማ በሚባሉ ሁለቱ ኮንፌዴሬሲዮኖች ሥር ተደራጅተው ቀደም ሲል የተነጠቁትን ይዞታቸውን ለማስመለስ ወደ መሃሉና ሰሜን

ኢትዮጵያ የተንቀሳቀሱበት ወቅት ነበር እንጂ ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጡበት አለመሆኑን መታወቅ ይገባል፡፡ ለዚህም የኘሮፌሰር መሐመድ ሀሰን "The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860" የሚል መጽሐፍንና ቀደም ሲል የተጠቀሰውን በኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በቅርቡ የታተመውን "የኦሮሞ ታሪክ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን" የሚል መጽሐፍ ማንበቡ በቂ ይመስለናል፡፡ አንብበው እንደሆነ መልሰው መላልሰው ቢያጤኑት መልካም ነው፡፡

በመጽሐፉ ገጽ 9 ላይ አማርኛና ጋልኛ አንድ ናቸው አብረው የሰፈረ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ሲዳማ እቤቱ ውስጥ የራሱ ቋንቋ ሲናገር በውጪ አማርኛ ይናገራል ብለውናል፡፡ እያወቁ እንዳላወቁ የጻፉት ኘሮፌሰሩ አማርኛና ኦሮምኛ ከተለያዩ ዘር ግንድ የመጡ አማርኛ ሴማዊ ሲሆን ኦሮምኛ ኩሻዊ ነው፡፡ ስለዚህ በቅርጽም በይዘትም አንድ አይደሉም፡፡ እርስዎ የሚናገሩት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአማራ ገዥ መደቦች ቋንቋ የበላይነት ለማስፈን ሲሉ በትምህርት ቤትና በሌሎች የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ብሔራዊ ቋንቋ በማድረግ በውዴታ ሳይሆን በግዴታ እንዲማሩና እንዲሠሩበት በመደረጉ ካልሆነ በስተቀር ኦሮሞም ሆነ ሌሎች የኩሽ ሕዝቦች በውስጥም ሆነ በውጪ መግባቢያ የራሳቸው ቋንቋዎች አላቸው፡፡ በዚሁ መጽሐፍ ገጽ ተከታታይ አንቀጽም ደራሲው ከ16ኛውመቶ ክፍለ ዘመን በፊትም (ማለትም "ዘመናዊቷ" ኢትዮጵያ ከመመሰረቷ በፊት) አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ ነበር በሚለው ፍልስፍናቸው ኢትዮጵያ የአንድ ብሔርና ቋንቋ እንደሆነች አድርገው ሊያሳምኑን ይሞክራሉ፡፡ ሀቁ ግን በኃይል የተመሰረተችው "ዘመናዊቷ " ኢትዮጵያ የአንድ ብሔር አገር ሳትሆን የራሳቸው ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ ያላቸው የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አገር ነበረች ናትም፡፡ ዛሬም ያለው ይኸው ነው፡፡ በሌላው በኩል ደራሲው በገጽ 102 እና 103 መጽሐፋቸው ላይ 'ጋላ' ስድብ ነው ወይ? የሚለውን የራሳቸው የተሳሳተ አመለካከት በጥያቄ መልክ አስቀምጠዋል፡፡ እንዲያውም ለአንድ ሕዝብ ስም የሚሰጠው ተጠሪዎች በሰየሙበት ወይም ከቋንቋ መዝገብ ተመርጠውለት ነው ይላሉ፡፡ በአንደኛ ደረጃ የኦሮሞ ሕዝብ ራሱን 'ጋላ ' ብሎ የጠራበት ጊዜ የለም፡፡ ምናልባትም የገዥ መደቦች የሰጡት ቃል እየቆየ ሲመጣ እንደራስ ስም እየመሰላቸው እኔ " ጋሊቲ" ብለው የሚመጻደቁበት እምነት ከቁጥር የማይገቡ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ መላው የኦሮሞ ሕዝብ 'ጋላ' የሚለውን ተቀብለዋል ከሚል ድምዳሜ ሊያደርሰን አይችልም፡፡ በተረፈ ስም የሚያወጣው ባለቤቱ ነው እንጂ ሌሎች ከመዝገብ ቋንቋ መርጠውለት አይደለም፡፡ በኦሮሞም ሆነ በሌሎች ሕዝቦች ባህል ስም የሚሰጠው በቤተሰብ፣ በሕብረተሰብ፣ በወላጅና ዘመድ አዝማድ እንዲያውም ብዙውን ጊዜ በአጉትና በአክስት ነው፡፡ በኦሮሞ ብሔር ውስጥ በገዳ

ሥርዓት ደንብ የስም አወጣጥ አለ፡፡ ይህ በቦረናና ጉጂ ኦሮሞች አሁንም በሰፊ ይሰራበታል፡፡

ስለዚህ ደራሲው 'የሞጋሣ' ሥርዓት ያካተተ የአስማሮም ለገሠን "Gada: Three Approaches to the Study of African Society" 1973 የሚለውን መጽሐፍና ሌሎችንም መጻሕፍት እንዲያነቡ ምክራችንን እንለግሳለን፡፡ ይህ ካልን በኋላ ግን ስም አውጪ የራሱን ስም በሕጋዊ መንገድ ለራሱ ሊሰጥም ሊቀይርም ይችላል፡፡ ይህ በዘመናዊ ሕግና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥም ያለ ነው፡፡ ስለዚህ የኦሮሞ ሕዝብ ኦሮሞ ነኝ እንጂ 'ጋላ' አይደለሁም ሲል የለም 'ጋላ ' ነህ አለበለዚያ ወደ ተገንጣይ ኦሮሞ ትፈረጃለህ ብለው አስተያየት መስጠት የትምክህተኝነት አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ከፕሮፌሰሩ አባባል የሚገርመው ደግሞ ኦሮሞች 'ጋላ' መባልን እንደማይወዱት ሁሉ አማሮችም አማራ ተብለው መጠራት አይፈልጉም ይላሉ፡፡ ለዕውነት ብንናገር አማራ ሆኖ አማራ አይደለሁም አማራ ብለህ አትጥራኝ ያለውን ግለሰብም ሆነ ሕዝብ አላየንም፡፡ እንዲያውም ሲሞካሽበትና ሲኩራራበት "ቆፍጣና" አማራ እያለ ሲፎክርበት የሚታይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የተባለ ስያሜም ቢሆን የጥንት ኩሽ ሕዝቦች ስም ለመሆኑ ከላይ በመገለጹ አንመለስበትም፡፡ ነገር ግን ከሰሎሞናዊ ሥረወ - መንግሥት (Solomonic Myth) ነን ባዮች ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑንና ይህም ቀደም ሲል በ3ኛው መቶ ክፍለ - ዘመን ንጉሥ ኢዛና የተጠቀሙበት እንደሆነ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ የመጨረሻው ሰሎሞናዊ ሥረወ - መንግስት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን እስከተወገዱ 1967 ዓ.ም ድረስ ለሚገዛቸው ሕዝቦች አገር ስያሜ አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡ እዚህ ላይ መጤን ያለበት መሠረታዊ ጉዳይ የሰሎሞናዊ ሥረወ-መንግሥታት ሥልጣናቸውን መለኮታዊ (Mandate from Heaven) ለማድረግ ኢትዮጵያና ሰሎሞናዊነትን የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታ አድርገው መጠቀማቸው የተለመደ የፖለቲካ ቅጥፈት መሆኑ ነው፡፡ ፕሮፌሰር! ይህንንም በጥልቀት እንዲፈትሹ እንደራስዎ ላሉት ተመራማሪዎች ትተነዋል፡፡

በሌላ በኩልም የኦሮሞ ሕዝብ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ በሚል ሽፋን መሞቱ፣ መገደሉና መረሸኑ አምላክ የቸራቸው እጆቹና ጡቶቹ በግፍ መቆረጡ የትላንት የአኖሌን የአርከና ሐርመ ሙራ ትዝታ ሲያስታውስ ይበግናል እንጂ ኢትዮጵያዊነትን አልጠላም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቆዩ የግሪክ እስክሪፕቶች (scripts)

'ኢትዮጵያ' የሚለው ስያሜ የኩሽ ሕዝቦች የጥንት መጠሪያ እንደነበረ ሁሉ ከኩሽ ሕዝቦች ደግሞ ኦሮሞ አንዱ በመሆኑ ለሕልውናው አደጋ ካልሆነ በስተቀር ሰው የራሱ የሆነውን እንደማይጠላ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል።

ደራሲው በመጽሐፋቸው ገጽ 103 ላይ እንዲህ ይላሉ "ጀርመኖች ጀርመን አትበሉን፣ ስዊድኖች ስዊድን አትበሉን አይሉም። ሁሉም በመሰላቸው ቢጠሯቸው ይቀበላሉ" ይላሉ። እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባ ጉዳይ ጀርመኖች ጀርመን ስዊድኖች ስዊድን ተብለው በመጠራታቸው ለምን ይቃወማሉ? እኛም ያልነው ይህንኑ ነው። ኦሮሞ ነንና ኦሮሞ ብላችሁ ጥሩን ነው የምንለው። ወረድ ብለውም "እርግጥ አንድ ሰው በኦሮምኛ ቋንቋ ሲነጋገር 'ጋላ' ቢል አያምርበትም ይሆናል" ብለዋል። እኛ የምንለው የስያሜ ማማር ወይም አለማማር ሳይሆን የስድብ ቃል ነው ብለናል።

በገጽ 109 መጀመሪያ አንቀጽ ላይ በኦሮሞ ታሪክ ላይ የጻፉትን የምዕራባውያን ተመራማሪዎችና "... በሚሲዮናውያን ያደጉ ለኦርቶዶክስ ክርስትና ጥላቻ የሚሰማቸው የኢትዮጵያ ሕዝብና አገሪቱን በድለዋል" ብለዋል። ለመሆኑ በደሉ ምን እንደሆነ በዝርዝር ቢያስቀምጡ መልካም ነው። እውነተኛ የኦሮሞ ሕዝብ ባህልና ታሪክ መጻፉ ነው ወይ? ባለታሪኩ የሆነውን የኦሮሞ ሽማግሌዎችን ጠይቀው ስለኦሮሞ ሕዝብ መጻፍ የታሪኩ ዕውነተኛነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ይመስለናል። ምክንያቱም ከታሪክ ዋና ምንጮች አንዱ የትውፊት (Oral Tradition) መረጃ ነውና። በትውፊት የተገኘው ማስረጃ ማመሳከር አለመቻል ደግሞ የእናንተ ችግርና ትምክህተኝነት ባህሪያችሁ ነው።

በመጨረሻም ፍጹም በማያወላዳ ሁኔታ ይህ መጽሐፍ የሚያስረዳ ነገር ቢኖር ደራሲው የጥንቶቹ ደብተራዎች ከገዥ መደቦች ጋር እጅና ጓንት ሆነው የኢትዮጵያን ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ለማስገበር በተለይም የኦሮሞን ሕዝብ በኃይል አንበርክኮ ባህሉንና ታሪኩን ለማጥፋት የአደረጉትን ገድሎች ለማወደስና ለማድነቅ ነው። መጽሐፉም የታሪክ አጻጻፍ ሥልት ዕውቀት /Historiographic Knowledge/ የጐደለው የተረት ተረት እንቶቅልሽ ድርሰት ነው። በተጨማሪም ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ትግልና መስዋዕትነት በአገኙት ዲሞክራሲያዊ ጮራ በመጠቀም የማንነታቸው መገለጫ የሆኑትን ባህሎቻቸውንና ቋንቋዎቻቸውን ከተቀበሩበት አዘቅት አንስተው ለማሳደግና ለማጐልበት የጀመሩትን ለመግታትና ለማጨናገፍ ብሎም ለመቀልበስ የተደረገ ሴራና ዳግም ዘመቻ ነው ለማለት ይቻላል። ይህ በትምክህት የተሞላ ስውር ተንኮልና መሠሪ አካሄድ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝቦችም

ሆነ ለአገሪቷ አንድነት ፣ ዕድገትና ልማት የሚፈይደው  አንዳችም ነገር የለውም ፤ አይኖረውምም።

ይልቁንስ በዛሬዪቱ ዓለም የሕዝቦችን መብትና ነጻነት የመጋፋት ዘመቻ ተዋናይ /ፊታውራሪ/ ከመሆን መቆጠብ ያሻል። አንዱ ያንዱን ባህል ፣ ቋንቋና ታሪክ ከመናቅና ከማንቋሸሽ ይልቅ ልዩነት መኖሩን አምኖ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላም ወረዶ ሕዝቦች በመከባበር ፣ በመፈቃቀር፣ በመፈቃቀድ፣መተሳሰብና በመቻቻል በወንድማማችነት አብረው የሚኖሩባት ኢትዮጵያን በመተማመን ዕውን ማድረግ ለሁላችንም የአገሪቷ ዜጎች የሚጠቅም መሆኑን አያጠያይቅም።